“የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እንዴት ይሆንልኛል?
ሉቃስ.ምዕ.1ቁ43-44

## <u>“ምነው በእናቴ ላይ ተነሳችሁ?”</u>

ምነው በእናቴ ላይ ተነሳችሁ?
ከቶ ምኗ ነው ቅር ያላችሁ?
ስሟን መጥራት ያቃታችሁ።
በወርቅ ልብስ ተጐናፅፋ
በቀኝ በኩል መቆሟ (መዝሙር44(45)ቁ9-17)
ንግሥት ተብላ መጠራቷ
ለልጅ ልጅ ሁሉ መትረፏ
የአባቷን ቤት መርሳቷ
በንጉሡ ፊት መወደዷ
በጌታዋ መመረጧ
በዳዊት አፍ መነገሯ
**ይኼ ይሆን ጥፋቷ**
**ፈልጋ እኛን ማግኘቷ።**
እህቴ ሙሽራ እያለ
እንደ ጨረቃ መዋቧን (መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን ምዕ6ቁ10)
እንደ ፀሐይ መጥራቷን
ዓላማ ይዛ መሰለፏን
በሰሎሞን አንደበት መገለጿ
**ይኼ ይሆን ጥፋቷ**
**ፈልጋ እኛን ማግኘቷ**
የደስታችን መፍለቂያ
የአዳኛችን ክርስቶስ መውጫ
የተዘጋች የምሥራቅ በር (ትንቢተ ሕዝቅኤል ምዕ44ቁ1-3)
ነቢያት የወደዷት
አስቀድመው ያከበሯት
ዘርን ባያስቀርልን ኖሮ (ትንቢተ ኢሳይያስ ምዕ1ቁ9)
እንደ ሰዶም በሆንን
እንደገሞራም በመሰልን
እያለ ኢሳይያስ ማድነቁ
ስሟን ማንሳቱ ማሞገሱ
**ይኼ ይሆን ጥፋቷ**
**ፈልጋ እኛን ማግኘቷ።**
እጁን ወደ አሕዛብ አንስቶ
ዓላማውን ወደ ወገኖቹ አቁሞ
ነገስታቱን አስደግድጐ

እቴጌዎችንም ዝቅ አድርጎ
በግንባራቸው እንዲሰግዱ (ትንቢተ ኢሳይያስ ምዕ49ቁ22-23)
የእግሯንም ትቢያ እንዲልሱ
እግዚአብሔር በነቢዩ ላይ አድሮ
ሲናገር መሰማቱ
**ይኼ ይሆን ጥፋቷ**
**ፈልጋ እኛን ማግኘቷ።**
የቅዱስ ገብርኤል ሰላምታ
የድምፁ ማማር እርጋታ (ሉቃስ ምዕ1ቁ26-36)
የትህትናው ከበሬታ
መልካም ዜና የብሥራቷ
ሰላም ላንቺ ይሆን እያለ
ከሴቶች መካከል መለየቷን
ጸጋ ሲሞላባት መታየቷን
እያረጋጋት ማመስገኑ
**ይኼ ይሆን ጥፋቷ**
**ፈልጋ እኛን ማግኘቷ።**
ዮሐንስ በማህፀን መዝለሉ
እያወደሳት መስገዱ
ኤልሳቤጥ በታላቅ ድምፅ (ሉቃስ ምዕ1ቁ39-47)
በመንፈስ ቅዱስ ተሞልታ
ስታመሰግናት መሰማቷ
**ይኼ ይሆን ጥፋቷ**
**ፈልጋ እኛን ማግኘቷ።**
በዚያ ሠርግ ቤት
በቃና ዘገሊላ
የሚላችሁን አድርጉ
እያለች መለመኗ መማፀኗ
ምልጃዋን ፈጥኖ ተቀብሎ (የዮሐንስ ወንጌል ምዕ2ቁ1-11)
ጋኖቹን ወኃ እንዲሞሉ
ማዘዙ መናገሩ ማሳየቱ
ቃልሽ ቃሌ እኮ ነው
እያለ ማስረዳቱ
ከእናቱ ጋር በበረከት
ዶኪማስን መጎብኘቱ
ዕድምተኞችን ማስደሰቱ
የተአምራቱ መጀመሪያ
ሲያደርጋት ልጁ መርጦ
ውኃውን ወደ ወይን ለውጦ
**ይኼ ይሆን ጥፋቷ**

**ፈልጋ እኛን ማግኘቷ።**
በእግረ መስቀል ስር ተቀምጣ
ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ? እያለ
አሰምቶ ሲናገር
በሥጋ ሆኖ ሕመሙን ሲገልፅ
የልጇን የጌታዋን መከራ
መስማት ማየቷ መጨነቋ
ለዮሐንስ እናትነት መመረጧ (**የዮሐንስ ወንጌል ምዕ 19፥26-27**)
እነሆ እናትህ ተብላ መሰጠቷ
**ይኼ ይሆን ጥፋቷ**
**ፈልጋ እኛን ማግኘቷ፡**
የሰኔ ጎልጎታ ጸሎቱ
የመልክአ ማርያም በረከቱ
የቅዳሴ ማርያም ሥርዐቱ
ነፍስን የሚያረሰርሰው ሰዓታቱ
የተአምረ ማርያም መጣፈጡ
ለእግዚአብሔር ሰው ምኞቱ
ለበጎ ነገር ትጋቱ
ልብን ለማቅናት ውጤቱ
ተግሳጽ ለማግኘት በትምህርቱ
ለጽድቅ መንገድ ትሩፋቱ
እንደሚጠቅም ማሰማቱ
ሐዋርያው ጳውሎስ በመልእክቱ (**2ኛ ጢሞ.ምዕ3፥14-ፍጻሜው**)
ለጢሞቲዎስ ማስረዳቱ
**ይኼ ይሆን ጥፋቷ**
**ፈልጋ እኛን ማግኘቷ።**
ዮሐንስ በፍጥሞ ደሴት
ራዕዩ ተገልፆለት (**የዮሐንስ ራእይ ምዕ12፥1-6**)
ታላቅ ምልክት ማየቱ
ስለ እመቤቴ ማነሳሳቱ
ፀሐይን ተጐናጽፋ
ጨረቃን ከእግሯ በታች አስገዝታ
የአሥራ ሁለት ከዋክብት አክሊል ደፍታ
አሕዛብን ሁሉ በብረት በትር
የሚገዛውን ወንድ ልጅ
ወለደች ብሎ መናገሩ
**ይኼ ይሆን ጥፋቷ**
**ፈልጋ እኛን ማግኘቷ።**
ከያዕቆብ ድንኳኖች ይልቅ (**መዝሙር 86(87)፥2-3**)
እግዚአብሔር ጽዮንን መውደዱ

ለዘላለም ማረፊያ (መዝሙር131(132)ቁ13-14)
የመረጥኳት ማደሪያዬ
እያለ ማሰማቱ
ዳዊትን ማፅናናቱ
ይኼ ይሆን ጥፋቷ
ፈልጋ እኛን ማግኘቷ።
ምነው በእናቴ ላይ ተነሳችሁ?
ከቶ ምን ነው ቅር ያላችሁ?
ስሟን ለመጥራት ያቃታችሁ?
በሉ እንግዲህ ልብ ይስጣችሁ
ቅዱስ ገብርኤል ይራዳችሁ (ሉቃስ ምዕ1ቁ28-29)
ወላዲተ አምላክን ያሳያችሁ
ስሟን አጣፍጦ ይንገራችሁ
የሰላምታ ድምጿን ታሰማችሁ (ሉቃስ ምዕ1ቁ39-41)
መንፈስ ቅዱስ እንዲሞላባችሁ (ሉቃስ ምዕ1ቁ41-46)
ኤልሳቤጥን ዮሐንስን ታድርጋችሁ
ብፅዕት በሉኝ ትበላችሁ። (ሉቃስ ምዕ 1ቁ48-49)

ከኃይለመስቀል ተስፋዬ
ለንደን 2003 ዓ/ም